# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

| | | |
|---|---|---|
| 1[ki] Diro Kiiro 8<br><br>Hawassa, Ella 29, 2012 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Alaalshi Hunda Fulinoho<br><br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፰<br><br>ሀዋሳ ሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም |



**Amado**

**Lallawu Kiiro 8/2012**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Rosamino Mootimmate Loosira Albi Qoqqowinni Fultino lallawubba Loosu aana Hosansa sufantanno Gede Fajjate Lallawa ……………………. Qoola ….**

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፰/፳፻፲፪**

**በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለመደበኛ መንግስታዊ ሥራዎች በነባሩ ክልል የወጡ አዋጆች ተፈጻሚነት እንዲቀጥል ለመፍቀድ የወጣ አዋጅ ………… ገጽ ….**


## LALLAWU KIIRO 8/2012

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Rosamino Mootimmate Loosira Albi Qoqqowinni Fultino Lallawubba Loosu Aana Hosansa Suffanno Gede Fajjate Fulino Lallawa**

Haaro Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma tantanantunkunni harancho yanna ikkasse kainohunni rosamino mootimmate looso loosate hasiisanno addi addi seerubba fushshe loosu aana hosiisate ledote yanna hasi’rannoha ikkasinninna seeriweelo mootimmate looso massaga dandiinannikkiha ikkinohura;

## አዋጅ ቁ ፰/፳፻፲፪

**በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለመደበኛ መንግስታዊ ሥራዎች በነባሩ ክልል የወጡ አዋጆች ተፈጻሚነት እንዲቀጥል ለመፍቀድ የወጣ አዋጅ**

አዲሱ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተደራጀበት ጊዜ አጭር ከመሆኑ የተነሳ መደበኛ መንግስታዊ ሥራዎችን ለማስኬድ የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ሕጎችን በማዘጋጀት ሥራ ላይ ለማዋል ተጨማሪ ጊዜ የሚፈልግ ሆኖ በመገኘቱ እንዲሁም ያለ ሕግ ማዕቀፍ መንግስታዊ ሥራዎችን መፈጸም አዳጋች በመሆኑ፣

Qoqqowunniha rosamino mootimmate looso loosate hasiisanno addi addi seerubba qinaawino garinni qixaabanninna kaajjitanni horote aana hossa geeshsha albi Wodiidi Daga, Dagoominna Manni Qoqqqowi Mootimmanni rosamino moottimmate loosira fulte horote aana noo seerubba haaro Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma giddo loosoho horonsi’nanni gede fajjanno seeri fula noosi daafira;

Ledeno, haaru Qoqqowira uuritanno jeefisiisaano uurinshuwa Qoqqowu giddo heedhanno gashshootu taqqara kaajjite uurritta geeshsha albi jeefisiisaano uurinshuwa tantano boode yannara sufanno gede jeefisiisaano bisubba uurrisano, biilloonynisanna loosu qeechansa muranno seerira worronnihu ledo sumuu yaano garinni loosu aana hosiisa hasiissannota ammanatenni Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Bayriidi Seeri quwa 48 cinaancho quwa 3 fidale ‘a’ garinni konni woroonni nooha lallambonni.

1. **Harancho Su’ma**

   Konne lallawa **“Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Rosamino Mootimmate Loosira Albi Qoqqowinni Fultino lallawubba Loosu Aana Hosansa Suffanno Gede Fajjate Fulino Lallawi Kiiro 8/2012”** yine woshshinara dandiinanni.

በክልሉ ለመደበኛ መንግስታዊ ሥራዎች የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ሕጎች በተደረጃ ሁኔታ እየተዘጋጁ እና እየጸደቁ ሥራ ላይ እስከሚውሉ ድረስ በነባሩ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ለመደበኛ መንግስታዊ ሥራዎች ወጥተው በሥራ ላይ የሚገኙ ሕጎች በአዲሱ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ተፈጻሚነታቸው እንዲቀጥል የሚፈቅድ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፣

በተጨማሪም በአዲሱ ክልል የሚቋቋሙ አስፈጻሚ አካላት በክልሉ ውስጥ በሚገኙ በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች በተጠናከረ አኳሄን እስከሚደራጁ ነበሩ የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ለተወሰነ ጊዜ እንዲቀጥል በአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ ህግ ላይ ከተደነገገው ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ በማመን በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ ፫ ፊደል ተራ ሀ መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

1 **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ **“በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለመደበኛ መንግስታዊ ሥራዎች በነባሩ ክልል የወጡ አዋጆች ተፈጻሚነት እንዲቀጥል ለመፍቀድ የወጣ አዋጅ ቁ. ፰/፳፻፲፪”** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2. Tiro**

**Qaalu horo wole tiro anno gede assa hoonguro konni lallawi giddo:**

1. “Rosamino Mootimmate Looso” yaa mittu mittunku seera jeefisiisaanncho woy seeri-tiraancho uurinshsha uurrinsoonnise hexxonna sokko jeefo ganate loosannoha giddonna uurrinshanniwa daanno owaataanchira owaante aate loonsanni loosooti.
2. “Albi Qoqqowo” yaa Wodiidi Daga, Dagoominna Manni Qoqqowooti.
3. “Haaru Qoqqowi” yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.
4. “Hasiisi garinni” yaa albi qoqqowinni fultino lallawubba su’minsa woy amadonsa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Moottimma ledo sumuu yitannonna loosu aana hossara dandiitanno bikkinni calla horote hossara hasiisannota xawissanno yaattooti.

**3. Loosu aana hosansa suffanno Gede Fajjantino Lallawubba**

Albi Qoqqqowi Mootimmanni rosamino moottimmate loosira fultinonna su’minsanna

**2 ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1 “መደበኛ መንግስታዊ ሥራ” ማለት እያንዳንዱ የመንግስት አስፈጻሚ ወይም ሕግ ተርጓሚ አካል የተቋቋመበትን ዓላማ እና ተልዕኮ ለማሳካት የሚሰራው የውስጥ እና ወደ ተቋሙ የመጣ ተገልጋይን ለማስተናገድ የሚፈጽመው ሥራ ነው፡፡

2 “ነባሩ ክልል” ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነው፡፡

3 “አዲሱ ክልል” ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፡፡

4 “እንደ አግባብነቱ” ማለት በነባሩ ክልል የወጡ አዋጆች ስያሜያቸው ወይም ይዘታቸው ከሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ጋር ሊጣጣሙና ተፈጻሚ ሊሆኑ በሚገባቸው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ ሊውሉ እንደሚገባ የሚገልጽ ሐረግ ነው፡፡

**3 ተፈጻሚነታቸው እንዲቀጥል የተፈቀዱ አዋጆች**

በነባሩ ክልል መንግስት መደበኛ መንግስታዊ ሥራዎችን ለማስኬድ የወጡና ስማቸውና

kiironsa konni lallawi ledo jeefote amadisiinsoonni lallawubba hasiissu garinni haaru qoqqowi giddo loonsanni rosamino mootimmate loosira horote aana hosansa suffanno gede konni lallawinni fajjinoonni.

## 4. Horoonsha Lainohunni

Konni lallawi quwa 3 garinni loosu aana hosansa suffara fajjinoonni albi qoqqowira fultino lallawubba loosu aana hossanno mami-geeshshi, jeefisiisaano uurrinshubba tantano, gashshootu taqinni, hajote amadonna hasiisaanchimma haaru qoqqowira ikkitanno jeefishshu bikkinni, jeefisate uurrinsoonni uurrinshuwa tantano, loosu aana noo gashshootu taqqaranna hajote danininna hasiishshi bikkinni horote hossannore ikkitanno.

## 5. Fajjate Wodhonna Biddissa Fushsha Lainohunni

1. Konni lallawira quwa 3 aana worronni garinni looso aana hosansa suffanno gede fajjinoonni lallawubba gumulsiisate woy haaru qoqqowira rosamino mootimmate loosira hasiishshu noonsari albi qoqqowira fultino wodho haaru qoqqowi giddo loosu aana hosansa suffanno gede fajjitanno wodho jeefisiisaanote amaale mininni fultanno.

ብዛታቸው ከዚህ አዋጅ ጋር አባሪ የተደረጉ አዋጆች እንደ አግባብነታቸው በአዲሱ ክልል አማካይነት ለሚሰሩ ለመደበኛ መንግስታዊ ሥራዎች ተፈጻሚነታቸው እንዲቀጥል በዚህ አዋጅ ተፈቅዷል፡፡

## 4 አጠቃቀምን በሚመለከት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ መሰረት ተፈጻሚነታቸው እንዲቀጥል የተፈቀዱ በነባሩ ክልል የወጡ አዋጆች ከተፈጻሚነት ወሰን፣ ከፈጻሚ ተቋማት አደረጃጀት፣ ከአስተዳደር እርከን፣ ከርዕሰ ጉዳዩች ይዘትና አግባብነት አንጻር ለአዲሱ ክልል በሚመጥን የተፈጻሚነት ወሰን፣ ልፈጽሙ በተቋቋሙ ተቋማት አደረጃጀት፣ ሥራ ላይ ባሉ የአስተዳደር እርከኖች እና እንደ ርዕሰ ጉዳዩ አግባብነት መጠን ጥቅም ላይ የሚውሉ ይሆናል፡፡

## 5 የመፍቀጃ ደንብና መመሪያ ስለማውጣት

1 በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ ላይ በተደነገገው መሠረት ተፈጻሚነታቸው እንዲቀጥል የተፈቀዱ አዋጆችን ለማስፈጸም ወይም ለአዲሱ ክልል ለመደበኛ መንግስታዊ ሥራ አግባብነት ያላቸው በነባሩ ክልል የወጡ ደንቦች በአዲሱ ክልል ውስጥ ተፈጻሚነታቸው እንዲቀጥል የሚፈቅድ ደንብ በመስተዳደር ምክር ቤት ይወጣል፡፡

2. Konni lallawi quwa 3 woy konni quwi cinaanchu quwi 1 garinni albi qoqqowira fultino lallawubba woy wodho jeefisiisate fultino biddissuwa woy haaru qoqqowira rosamino mootimmate loosira hasiishshu noonsa biddissuwa haaru qoqqowi giddo loosu aana hosansa suffanno gede fajjanno biddissi mitte mittente jeefisiisaancho uurrinshanni fulanno.

**6. Lallawu Kajjanno Yanna**

Kuni lallawi Ella 29 barrinni 2012 M.D hanafe kaajinoha ikkanno.

Hawaasa, Ella 29, 2012 M.D

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Perezidaanticha**

2 በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በነባሩ ክልል የወጡ አዋጆችን ወይም ደንቦችን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች ወይም ለአዲሱ ክልል ለመደበኛ መንግስታዊ ሥራ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች በአዲሱ ክልል ውስጥ ተፈጻሚነታቸው እንዲቀጥል የሚፈቅድ መመሪያ በእያንዳንዱ አስፈጻሚ ተቋም ይወጣል፡፡

**6 አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ሀዋሳ፣ ሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም

ደስታ ሌዳሞ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳደር

**Albiidi Qoqqowinni Fultinonna Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Giddo Suffe Loosu Aana Hossara Fajjinoonni Lallawubba Su’manna Kiiro Xawissanno Shae**

| A.K | Lallawu Su’ma | Addi Xawishsha |
|---|---|---|
| 1 | Moottimmate Loosaasine Lallawi K.175/2011 | |
| 2 | Taksete Gashshooti Lallawi K. 166/2009 | |
| 3 | Eote Giwiri Lallawa K. 165/2009 | |
| 4 | Qoqqowu Yoo Minnara Loossanno Ayyaayyamaanonna Hojji Seeru Hajo Borreessaanora Loosu Fajjo Aatenna Gashshate Lallawi K. 164/2008 | |
| 5 | Gatona yaate Amanyooti Lallawa K. 157/2007 | |
| 6 | Biilloonyunni Ka’ino Aliidi Deerri Biilto, Seeri-Songote Miillanna Yooanote Qoossonna Horo Gumulate Fulino Lallawi K. 148/2004 | |
| 7 | Dubbu Latishshi, Agarooshshinna Horoonshi Lallawi K. 147/2004 | |
| 8 | Hidhotenna Jajju Gashshooti Lallawi K. 146/2004 | |
| 9 | Jirote Bikka Xawisanna Borreessiisate Lallawi K. 138/2003 | |
| 10 | Temberete Qaraxi Lallawi K. 135/2003 | |
| 11 | Ternoverete Takse Lallawi K.57/1995nna Woyyessinonni Lallawi K. 134/2003 | |
| 12 | Womaashshu Gashshooti Lallawi K. 128/2002 | |
| 13 | Baadiyyete Baatto Horoonsi’rate Baatooshshinna Giwirinnu Loosi Eo Giwiri Lallawi K.122/2000 | |
| 14 | Baadiyyete Baatto Gashshooti Lallawi K. 110/1999 | |
| 15 | Gutu Ijaari Annimma Lallawi K. 102/1999 | |
| 16 | Maatete Seeri Lallawi Kiiro 75/1996 | |

## በነባሩ ክልል የወጡና በሲዳማ ብሔራዊ ክልል ተፈጻሚነታቸው እንዲቀጥል

## የተፈቀዱ አዋጆች ስምና ብዛት የሚገልጽ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የአዋጁ ስም | ልዩ መግለጫ |
|---|---|---|
| 1 | የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁ.175/2011 | |
| 2 | የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁ.166/2009 | |
| 3 | የገቢ ግብር አዋጅ ቁ.165/2009 | |
| 4 | በክልሉ ፍርድ ቤቶች ስለሚሰሩ ጠበቆችና የግል የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁ.164/2008 | |
| 5 | የይቅርታ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁ.157/2007 | |
| 6 | ከኃላፊነት የተነሱ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁ.148/2004 | |
| 7 | ስለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁ.147/2004 | |
| 8 | የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁ.146/2004 | |
| 9 | ሀብትን ለማሣወቅና ለማስመዝገብ የወጣ አዋጅ ቁ.138/2003 | |
| 10 | የቴምበር ቀረጥ አዋጅ ቁ.135/2003 | |
| 11 | የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁ.57/1995 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁ.134/2003 | |
| 12 | የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁ.128/2002 | |
| 13 | የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር አዋጅ ቁ. 122/2000 | |
| 14 | የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁ.110/1999 | |
| 15 | የጋራ ሕንፃ ባለቤትነት አዋጅ ቁ.102/1999 | |
| 16 | የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ. 75/1996 | |